# <u>መቅሠፍተ-ዲሞክራሲ ፤</u>

የትግል መሪዎቹ ዲሞክራሲን ሊያለብሱኝ !
ከድድቅ ጭለማው ሕይወት ሊያላቅቁኝ
ወደ ብርሃን ዓለም ሊመሩኝ
የውሸት ተስፋ ሲያሰንቁኝ
አምኛቸው ነበር ከልቤ !
ይወገድ መስሎኝ የነፃነት ረሃቤ
ዲሞክራሲ መጣ ብለውኝ
ስብከታቸውን እንድሰማ ጠርተውኝ

ሁሉም ችግር ያልፋል !
ድኅነትም ይራገፋል !
በሰው ልጆች እኩልነት
ሠርቶ ለማደር በነፃነት
ዲሞክራሲው ይጠቅምሃል !
ተከፋፍሎ መኖሩ ይጎዳሃል !
አንድነቱ ይበጅሃል !!
ብለው በተናገሩት ባምናቸውም
ዕውነትን ከነሱ ዘንድ አላየሁም !
አንዳንዶቹም መሪዎች መገንጠልን አንግበው
ካልተገነጠልን ዲሞክራሲ የለም ብለው
ለሥልጣን የቋመጠ አንደበታቸው
ውስጤን መርዞ ስብከታቸው
አምኜያቸው ነበር ከልቤ !
ይወገድ መስሎኝ የነፃነት ረሃቤ !
በሁሉም አቅጣጫ ተዋከብሁ
ቅርሴን ለመቅ ሆዳቸው እያስረከብሁ
ብዙ ደከምሁ አብሬያቸው
ለካስ ከንቱ ነበር ሃሳባቸው !!
ግን በጣም የሚገርመው
የትግል መሪዎቹ ራሳቸው
የዲሞክራሲን ምንነት ያለማወቃቸው !
ኋላና ፊት መሆናቸው
እጅግ ያስገርመኛል ዛሬም
መቼም አልረሳው ለዘለዓለም
በዚያ አንካሳ ትግላቸው
ለወያኔው ዕድል መስጠታቸው !
ድርጊታቸው ይቆጨኛል
የዘወትር ጸጸት ተክሎብኛል

ወያኔዎችም የውሸቱን ዲሞክራሲ እየተገበሩ
ድሃውን ዜጋ በወኀኒ እያጎሩ
ዜግነት ካጎናጸፈው ርስቱ እያባረሩ
ርስቱን ለባዕዳን ሸጠው
ምስኪኑን ወገን ለስደት ዳርገው
ዲሞክራሲ የሚሉትን እንዳየነው
ለሌሎች ዓለማት ብርሃን ነው !
ለኛ ድድቅ ጭለማና መቅሠፍት ነው !!

አይ ዲሞክራሲ !!
ዲሞክራሲ ብሎ ነገር !
ሌላው ያደረገው እንዳይቀር
በስመ ሥልጣኔ የዲሞክራሲ ሽቀላ
ሕዝብን በግፍ ሲያጉላላ
ሳንተዋወቅ ተቃቅፈን !
ላንኳኋን ተለያይተን !
የዲሞክራሲን ጥቅም ሳናውቀው
ስሙን ከፍ አድርገን አራግበነው
የሀገር ሀብትና የሕዝብ ሕይወት ገበርነው !
እንኳንስ ለኛ በተስፋ ለቋመጥነው
ለቀጣይ ትውልድም መሠረት አሳጣነው !
አይ ዲሞክራሲ !!
ዲሞክራሲ ብሎ ነገር !
ሌላው ያደረገው እንዳይቀር
ያለው ላይቀር እንባ ቢፈስ
ወግ ነው ተብሎ የለ ሲዳሩ ማልቀስ ?
ዲሞክራሲው ሌሎችን ሲያኖር አቻ ላቻ
ምነው መቅሠፍት ሆነብን ለኛ ብቻ ?
ሀገር ማጥፊያና መራኮቻ ?
አንደበትን እየዘጋ እያቃተን መናገሩ !
ዓይኖቻችን ተሸፍነው ሲበዛብን ድንብርብሩ !
ዲሞክራሲው ተገልብጦ ሲራክሞዲ ሲሆንብን !
ይህን መዓተ-ቅስፈት ከቶ ማነው የሚያይልን ?
አይ ዲሞክራሲ !!
አሁንም አለሁ ይላል ዲሞክራሲ ? !
ለሌሎች ቅዱስ ሆኖ ለኛ ሆኖብን ከይሲ ? !
ሕዝብን በጠራራ ጸሐይ ገድሎ !
ካገር ከቀዬው ነቅሎ !
በስደት ዓለም አንቀዋሎ !
ሕፃን አዛውንት መድረሻ አጥተው !
በረሃብ ሕመም ተሠቃይተው !

አይ ዲሞክራሲ !!
አሁንም አለሁ ይላል ዲሞክራሲ ? !
ቅዱስ መስሎ ከይሲ !!

ምናልባት ቅዱስ ቢባል ዲሞክራሲው
እኛ ሳንሆን እንቀራለን ከይሲው ???!!!
በጥሩ አዕምሮ ማስተዋል ስላቃተን
መተግበር ስላልቻልን ተረጋግተን !!
አዎ ! ዕውነቱ ያ ይመስለኛል !
ዲሞክራሲው ከልብ ቢስተዋል
ፊታውራሪዎቹ ለሥልጣን ሳይቋምጡ
ሰብዓዊ መብትን ሳይረጋግጡ
የዲሞክራሲን ምንነት በውል ቢያስረግጡ
ነበር ቁምነገሩ ከዚያ ላይ
ለማቅለል የፍጡርን ሥቃይ !
ብናስተውል ካሳለፍነው
ድክመታችን ግልጽ ነው !
ከሥርዓተ-ፊውዳል ከባላባት
ከዓጼዎቹ ከነገሥታት
ከወታደራዊ አገዛዝ ከኮምዩኒስት
ከነፃው ገበያ ካፒታሊስት
ከማንም ከምንም አልተስማማን
ከዲሞክራሲው አልተጣጣምን
ታዲያ ምን ይሻላል ?
ምንስ ይበጃል ?
አዲስ ሥርዓትስ ከየት ይመጣል ?
ቢመጣስ ማን ይቀበላል ?
ሁሉ ሳይስማማን ሁሉን ነቅፈን
ተግባራዊ የምናደርገው ሥርዓት ከሌለን
ቀጣዩ ሕይወታችንን በእንዴት እንኖራለን ?
ምናልባት ቅዱስ ቢባል ዲሞክራሲው
እኛ ሳንሆን እንቀራለን ከይሲው ??? !!!!

<u>ከአቤ ኮስትሬ ፤</u>